| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ርእስ ፡ አንቀጽ ። |
| ርእስ ፤ | "ኅዳር ፡ ታጠነ!" |
| ደራሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | ታኅሣሥ ፡ 2013 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቍ.2013-002 |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

እግዚአናችንን ፡ የማስከበር ፥
ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ የመሥራት ፥
ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ የማቆም ፡
ሀገራዊ ፡ ዐላማችንን ፡ ለመፈጸም ፥ በኢትዮጵያና ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የምንገኝ ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችን ፡ ለኾነው ፡ ለኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ እናብር!
የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።
ሥልጡንሕዝብና ።
www.slttunhzb.net

# ርእስ ፡ አንቀጽ ።

editorial | éditorial | اِفْتِتَاحِي

## ኅዳር ፡ ታጠነ!

---

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ዐምባ ፡ ገነን ፡ ይዘት ፥ ላለፉት ፡ ወራት ፡ ቢያንስ ፡ በሦስት ፡ እና ፡ ባራት ፡ አንጃዎች ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ ተከፋፍሎ ፥ በማያባራ ፡ ጠብ ፡ ውስጥ ፡ ተዘፍቆ ፥ የይዘቱ ፡ ባለዐደራ ፥ ዐምዱና ፡ ምሰሶው ፡ ሕ.ወ.ሐ.ት ፡ (ሕዝባዊ ፡ ወያኔ ፡ ሐርነት ፡ ትግራይ) ፡ ተጨንቆ ፥ ድንገት ፡ በግልፍታ ፥ ራሱን ፡ በማጥፋት ፡ የተሸከመውን ፡ ሕንጻ ፡ ዐብሮ ፡ ሊንደው ፡ በመሻት ፥ ጥቅምት ፡ 24 ፡ ቀን ፡ 2013 ፡ ዓ.ም. ፥ መቀሌ ፡ ዐምባ ፡ ላይ ፥ ጥይቱን ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ ጠጣት ። ኅዳር ፡ በታጠነ ፡ በሳምንቱ ፥ ኅዳር ፡ 19 ፡ ቀን ፡ 2013 ፡ ዓ.ም. ፡ በጧቱ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ጠሮች ፥ ምልክዮሽ ፣ ፋሺዝምና ፡ አፓርትሀይድ ፡ ከነግስንግሱ ፥ በፍጡራቸው ፡ በሕ.ወ.ሐ.ት ፡ ጣረ ፡ ሞት ፡ በአማን ፡ በረሱ ፣ ተሻሩ ፥ መርዝና ፡ ጦሳቸው ፡ አንድጋ ፡ ረከሱ ።

ምሰሶው ፡ ተሰብሮ ፡ ተገምዶ ፤ ባዕድ ፡ ሠራሹ ፡ የጭቄና ፡ ሕንጻ ፡ ኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ተናጋ ፤ ግድግዳ ፡ እና ፡ ማገር ፡ ሲቀሩ ፥ ጣራው ፡ ከእነባጡ ፡ ተደረባ ። ምሰሶና ፡ ጣራ ፡ አልቦው ፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ቅሬታ ፡ ይዘት ፥ እንሆ ፥ «ዛሬ ፡ ... ፣ ነገ ፡ ... ፡ ይናዳል ፣ ይፈርሳል» ፡ ተብሎ ፡ ተሟረተበት ። ከእንግዲህ ፡ ሕንጻውም ፡ ሕንጻ ፡ አይኾን ፤ ኹሉም ፡ ፈርሶ ፡ በባለቤቱ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ባዲስ ፡ መሠረትና ፡ ባዲስ ፡ ዐቅድ ፡ ካልተሠራ ፡ በቀር ፥ ፈትም ፡ ቤቱ ፡ አልነበር ፥ ከንግዲህም ፡ ቤቱ ፡ አይኾን ❖


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2013 ፡ ዓ.ም. ።